ዳንኤል ሀይለ-ሚካኤል እና ሌሎች ከኒክ ኮንስታንቲኒዲስ እና ሌሎች ጋር
Daniel Haile-Michael & Ors v Nick Konstantinidis & Ors
VID 969 of 2010

በፕሮፌሰር ጎርዶን/ GORDON ና በዶ/ር ሀንስትሪድጀ/ HENSTRIDGE የመጀመሪያ ሪፖርቶች ላይ አጭር መግለጫ

መጋቢት/ March 2012 ዓ.ም ጥናት እንዲካሄድ የተሰጠውን ትእዛዝ በመከተል፤ ስምንት ተጠያቂዎች ብዙ ፋይሎችን እንዳዘጋጁና፤ ይህም በፍለሚንግቶን ወይም በኖርዝ መልበርን ከ2005 እስከ 2008 ዓ.ም ለሚኖሩ ወንዶችና በጥር/January 1 ቀን 1987 ዓ.ም እና በጥር/January 1 ቀን 1993 ዓ.ም መካከል የተወለዱ ታዳጊ ከ2005 እስከ 2008 ዓ.ም ባለው ጊዜ ከቪክቶሪያ ፖሊስ መኮንን ጋር ተጽእኖ ችግር ላጋጠማቸው ከቪክቶሪያ ፖሊስ የፈጣን ለውጥ ፍተሻ/ LEAP መረጃ ፋይሎች ውስጥ ስታትስቲክ የጥናት መረጃ ያካትታሉ። ፕሮፌሶር ጎርዶን/Gordon በዚህ መረጃ ጥናት አካሂዶ የሚከተለውን አግኝቷል:

(a) የአፍሪካ ጎሳ ወንዶች በፈጣን ለውጥ/ LEAP ፍተሻ መረጃ "የመስክ ጥየቃ/field contact" የተገኙት ከመቶ እጅ (43%) ሲሆን ይህም እንደ 2006 ዓ.ም ህዝብ ቆጠራ ጥሬ መረጃ (እሱም 18%) መሰረት በፍለሚንግቶንና በኖርዝ መልበርን ከሚኖሩት ተመሳሳይ ወንዶች ውስጥ የአፍሪካ ዘር ሀረግ 2.4 ጊዜ እንደበለጠ ነው።

በሌላ አገላለጽ፤ በተለይ ወንዶች የአፍሪካ ጎሳ በግምት ከሁለት ተኩል ጊዜ በላይ በበለጠ ከፖሊስ ጋር ግጭት በመፍጠር በፖሊስ ምዝገባ እንደተካሄደ እንጂ የነሱ ህዝብ እንደገለጸው ጉዳይ አይደለም።

ይህ በጥናት የተደገፈ መረጃ ጠቃሚና እንደ ፕሮፌሶር ጎርዶን አገላለጽ በዘፈቀደ የተመረጠ አይደለም። ዶ/ር ጆን ሀንስትሪድጀ ስታቲስቪያን በስምንተኛ እና በዘጠነኛና ተከሳሾች የቀረበ እንዳለ ሁኖ ከዚህ በታች ባሉ የጥናት ውጤቶች ይስማማል።

(b) በተለይ ለወንዶች የአፍሪካ ጎሳ አማካኝ የወንጀት ጥፋት (7.8 የሚሆን ወንጀል) ከሌላ የጎሳ ዘር (12.3 የሚሆን ወንጀል) በተለይ ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ እንደሆነ ነው። ይህ የጥናት ውጤት በስታቲስካል አገላለጽ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ፕሮፌሶር ጎርዶን በጥናት አረጋግጧል።

በሌላ አገላለጽ፤ በቪክቶሪያ ፖሊስ የፈጣን ለውጥ/ LEAP መዝገብ መሰረት፤ በአካባቢው ካሉት ከሌላ ጎሳ/ነገድ ከመጡት ወንዶች ጋር ሲነጻጸር በተለይ ወንዶች አፍሪካዊያን በአማካኝ ዝቅተኛ ወንጀሎች ፍጻሜ ክስ እንደቀረበ ነው።

በፕሮፌሶር ጎርዶን ጥናታዊ ውጤት ላይ ዶ/ር ሀንስትሪድጀ ተስማምቷል (ቢሆንም በስታቲስካል አገላለጽ ጠቀሜታ ባለ ልዩነት ጥያቄ ያቀርባል)።

(c) ከአፍሪካዊ ጎሳ በወንጀል የተከሰሰ ሲነጻጸር በተለይ ወንዶች በወንጀል የተከሰሱ አፍሪካዊ ያልሆኑ ጎሳዎች 8.5 ጊዜ የበለጠ "በመስክ ጥየቃ" ላይ ያልተገኙ ሲሆን፤ እንደ ፕሮፌሶር ጎርዶን አባባል የትኛው ጠንካራ ስታቲስካል ማመዛዘኛ ጠቀሜታ እንዳለው ነው። በፕሮፌሶር ጎርዶን ጥናታዊ ውጤት ላይ እንደገና ዶ/ር ሀንስትሪድጀ ተስማምቷል። ፕሮፌሶር አንድረው ጎልድስሚዝ/Andrew Goldsmith፣ የወንጀለኛ አጣሪ ባለሙያ ስምንተኛ እና ዘጠነኛ ተከሳሾች ባሉት እንደጻና ታዲያ የዚህ ስታቲስቲካል አገላለጽ እንደ መጀመሪያ ግንዛቤ ሆኖ "ፊት ለፊት ማጋጠም" ይሆናል።

(d) የተወሰኑ ወንዶች "በመስክ ጥየቃ" ላይ ተገንተው ከነበር በፕሮፌሶር ጎርዶን/ Gordon የጥናት ውጤት መሰረት በተለያየ ሁኔታዎች ላይ ከአፍሪካዊ ነገድ ጋር በተዛመደ ፖሊስ በሚጠቀመው ቃላት (being, "ወሮበላ መንጋ/gang", "ምክንያት የለሽ/no reason", "ያለ ምክንያት/nil reason", "ሂድ/move on", እና "አሉታዊ ባህሪ/negative attitude") እና ከተለያዩ ሁኔታዎች ባለ ፖሊስ እነዚህን የንግግር ቃላት ከሌላ ጎሳዎች ጋር ሲጠቀም ታዲያ በመካከላቸው ከፍተኛ የስታቲስቲካል ልዩነት እንዳለ ነው። በመቶ እጅ የመስክ ጥያቄ/ግንኙነት ማስታወሻ እንደሚያሳየው፤ በመስክ ግንኙነት ጊዜ እነዚህ ንግግሮች ከተወሰኑ ወንዶች አፍሪካዊያን ጎሳ ጋር በተዛመደ 16% ሲሆን ይህም ከሌላ ጎሳዎች ጋር ሲነጻጸር የሌላ ጎሳ ወንዶች 10% ነው።

በሌላ አገላለጽ፤ ከሌሎች ወንድ ጎሳዎች ጋር ሲነጻጸር፤ ፖሊስ ከተወሰኑ ወንዶች አፍሪካዊ ጎሳ ንግግር ሲያደርግ እነዚህን ቃላት በበለጠ መጠቀም እንደሚችል በስታቲካል የተደገፈ ነው።

በስታቲስካል አገላለጽ ጠቀሜታ ልዩነት ላይ ዶ/ር ሀንስትሪድጀ ጥያቄዎችን አቅርቧል፤ አለመጣጣም ልዩነት እንዳለ ተስማምቷል።